# ይድረስ ለአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ (ሀማ ቱማ)
# ለአቶ ጌታቸው ረዳ ጹሁፍ ምነው መልስ መስጠት ተሳነው ?

ያቶ ጌታቸው ረዳ ብዕር ሲያጋልጠዎ እንደ ሳዳም ሁሴን ሸሽተው ጉድጓድ ውስጥ ገቡ እንዴ ? መልስ አልሰጥ ያሉት ? በዚህ ዓይነትማ የሚያወሩትና የሚጽፉት እንዳው ዝም ብሎ የፈሪ ቱልቱላ ነው ማለት ነው።

ሰው መቼም አቶ ጌታቸው እረዳን እውነቱን የሚናገር ነው ብሎ ያምነዋል። እርሰዎ ግን ሲደነቁ አንሰማም። ድርጅተዎም ድሮ እንደ ሞተ ነው የሚወራው።የሙት ዓመት መታሰቢያም በየዓመቱ ይዘከራል። ሕዝቡ ይህን እያየ ጥቂቱ ነብስ ይማር ሲል አብዛኛውና የኢሕአፓ ሰው ያወግዛል ይራገማል።

በኢሕአፓ አመራር ውስጥ እርሰዎም ወንድመዎም ስለነበራችሁ መጨረሻ ላይ ኢህአፓ ሲሞት የድርጅቱን ገንዘብ ለግላችሁ አድርጋችሁታል እያለ ሰው ያማችኋል። ከወያኔ በፊት አማራውን ያጠቃው ኢህአፓ ነው ይላል አማራው። ቂምም ይዟል። ኢህአፓ ያማራውን ገበሬ መንደር ሲያቃጥል፣ ሚስቱንና ሴት ልጆቹን ሲደፍር፣ ከብቱን ሲዘርፍ፣ እህሉን ሲወስድ በጥይት ሲረሽን ተደብቀን ዓይተናል፣ መልካቸውንም አንረሳም የሚሉ  የትናንት ህጻናት አድገው እርሰዎ እውነቱን እንዲያምኑና ሕዝቡን ይቅርታ እንዲጠይቁ እየጠበቁ ነው።ሰው የማያውቀው ነገር የለምና ገና ብዙ ጉድ አለ። እርሰዎ ባይናገሩት ወደፊት መጻሃፍት በየመልኩ ያወጡታል።

አቶ ጌታቸው ረዳ የጠየቀዎት ሁለት ነገሮችና ናቸው። አንዱ በማስረጃ ለጻፍኩት መልስ በመረጃ የተደገፈ መልስ ስጠኝ ነው። ሁለተኛው  አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ “ከመሞትህ በፊት ሃቁን ለኢትዮጵያ ሕዝብ መናገር ይኖርብሀል” ብሎ ነው የጠየቀው። ስለዚህ ሁሉን ነገር ግልጽ አርገው በይፋ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይናገሩ፣ ይቅርታም ይጠይቁ።

ነገ ግን “የተዳፈነ እሳት የጠፋ ይመስል በኢሀአፓ ላይ ዘመቻው ተጧጧፈሳ” እያላችሁ ጥርስ የሌለው ፉከራችሁን፣ ሰው አንቅሮ የተፋውን ፌዛችሁንና ሸንገላችሁን ተው።

ከታማኝ ዘመነ